የሰ/መ/ቁ. 53844

ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጐስ ወልዱ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- አቶ ውጅራ ንዳ ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. አቶ ታደሰ መኮንን ጠበቃ ይመኑ ገ/ፃድቅ ቀረቡ

2. አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ሊቀመንበር ኪሮስ አምደየሱስ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ አንደኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆኑን ተከራክረዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በሥር ተከሳሽ የሆኑት አመልካች እኔ በሊቀመንበርነት የምመራው አዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር አለ በማለት ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ተቀብለው በመውሰድ በልጽገውበታል፡፡ ተከሳሹ /አመልካች/ ማስጠንቀቂያ ብጽፍላቸውም መልስ አልሰጡኝም ስለሆነም ከእኔ የወሰዱትን ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍሉ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች ገንዘቡን ለእኔ በግሌ አልሰጠኝም፡ ገንዘቡን የከፈለው ለቤት ሥራ ማህበር ሲሆን ገንዘቡን ለማህበሩ የከፈለ ስለመሆኑ ደረሰኝ ተሰጥቷል፡፡ እኔ ገንዘብ የተቀበልኩት በወቅቱ የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኔ ነው፡፡ ስለዚህ ክሱ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት አመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺ.ህ ብር/ ከግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አንደኛ ተጠሪን በአንደኛ መልስ ሰጭነት ሁለተኛ ተጠሪን በሁለተኛ መልስ ሰጭነት ስማቸውን በመጥቀስ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ገንዘቡን እኔ በግለሰብነቴ ሣይሆን የማህበሩ

ገንዘብ ያዥ ስለሆንኩ የተቀበልኩት መሆኑን ማስረጃ በማቅረብ ተከራክሬአለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛው ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ጠይቆ ገንዘቡ ለማህበሩ ገቢ መሆኑንና ገንዘቡ እኔን የማይመለከተኝ መሆኑን በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ ይህንን ሁሉ በማለፍ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ሁለተኛው ተጠሪ አለኝ የሚለውን የሰነድ ማስረጃ በማያያዝ በክርክሩ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ ሆኖ እንዲገባ ያመለከተ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ማህበሩ ህጋዊ ህልውና የሌለው መሆኑን በማረጋገጥ ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረበው አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ የከፈለ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው በአዲስ ዘመን 83 የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር ሥም የታተመ የገንዘብ መሠብሰቢያ ደረሰኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማህበሩ የራሱ የሆነ ማህደር ያለው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ቡራዩ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤትና የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ማህበራዊ ማደራጃና ማስፋፊያ መምሪያ የፃፉቸው ደብዳቤዎች ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ገንዘቡ የተከፈለው መሆኑንና ክርክሩ አመልካችን ሳይሆን በቀጥታ እሱን የሚመለከተው መሆኑን ገልፆ በሥር ፍርድ ቤት ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያመለከተ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትን መዝገብ በማስቀረብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛው ተጠሪ የከሳሽን /የአንደኛ ተጠሪን/ ክስና ማስረጃ ወስደው መልስ እንዲያቀርቡና በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ከፈቀደ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም በነበረው ቀነ ቀጠሮ መልስ ይዘው ባለመቅረባቸው የሁለተኛ ተጠሪን ጣልቃ ገብነት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 199 መሠረት ሠርዥዋለሁ በማለት ትእዛዝ የሰጠ መሆኑን ችሎቱ አስቀርቦ የሥር ፍርድ ቤት መዝገብና አመልካች በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ካቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የተከተለው የክርክር አመራር ሥርዓትና በመጨረሻም ውሳኔ ሲሰጥ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመመሥረት ጉዳዩን መርምረናል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ታህሣሥ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ያቀረቡትን አቤቱታ በመቀበል በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አመልካች ገንዘቡን የተቀበለው የማህበሩ ገንዘብ ያዥ በመሆኑና ማህበሩም ገንዘቡ ገቢ የተደረገለት በመሆኑ ከሳሽ /ሁለተኛ ተጠሪ/ ስለማህበር አባልነትና ተመላሽ ገንዘብ መከሰስም ሆነ መከራከር ካለበት ከማህበሩ ጋር መሆን አለበት የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ በሥር ከሳሽ ክስና ማስረጃ ይዘው እንዲቀርቡ በተቀጠረበት ቀን ካልቀረቡ የሁለተኛ ተጠሪን መልስ የመስጠት መብት በማለፍ ውሣኔ መስጠት ሲገባው ህጋዊ ህልውና አለህ በክርክሩ ጣልቃ እንድትገባ ተፈቅዷል ያለውን አካል ከክርክር ውጭ እንዲሆን የሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን መብት የሚያጣብብና አንድ በክርክር ተካፋይ የሆነ ሰው መልሱንና ማስረጃውን ባያቀርብ ፍርድ ቤቱ በሌለበት ክርክሩን ሰምቶ የሚወሰን መሆኑ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 70 የተደነገገውን የሚጥስና የክርክር አመራር ጉድለት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛ ተጠሪ ሕጋዊ ህልውና እንዳለውና በክርክር ጣልቃ መግባት እንደሚችል የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዛ ከሰጠ በኂላ ሁለተኛው ተጠሪ ህጋዊ ህልውና እንደሌለውና አንደኛ ተጠሪ በማህበሩ ስም የታተመ ደረሰኝ ተቀብሎ ለከፈለው ብር 20,000 /ሀያ ሺህ ብር/ አመልካች በግሉ ተጠያቂነት አለበት በማለት መጋቢት 16 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፍርድ ቤቱ የማህበሩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ስለመሆኑ ታህሳስ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ጋር የሚቃረንና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ሁለተኛ ተጠሪና በአንደኛ ተጠሪ መካከል የቀረበውንና የሚቀርበውን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ከሥር ፍርድ ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ